# ለፍትህ እንነሳ !

## (በኮለኔል መንግስቱና አገዛዙ ጥቃትና በደል ለደረሰባችሁ ዜጎች ሁሉ መልዕክትና ጥሪ )

ሰሞኑን  የደርግ አረመኔ መንግሥት ደጋፊዎች የመንግሥቱን መጽሐፍ በማሳተም አረመኔውን ለመጥቀም ቆርጠው ተነስተዋል። በተደጋጋሚ የሚያደርጉት ትክክል እንዳልሆነና ከወያኔ ዘረኛ መንግሥት ጋር የሚደረገውን ሃገር አድን ትግል እንደሚጎዳ በተለያየ መንገድ ቢነገራቸው አሻፈረኝ በማለት በትምክህት መጽሐፉን አሳትመው አረመኔውን ለመጥቀም ጥረት እያደረጉ ናቸው።

በጣም የሚያስገርመው ከአረመኔው ወንጀለኛ ጋር ተባባሪ ሆነው ከነበሩትና ታሪክን መካዳቸው የሚጠበቅ ከሆኑት በተጨማሪ አንድም ቀን እንኳን ይህ አረመኔ ለሠራው ግፍ ለፍርድ ይቅረብ ያላሉ ፣  በደርግ የተጨፈጨፉትን በሚመለከት ፍትህ ያልጠየቁ ፤ የግፉን ታሪክ ለማወቅ እንኳን ከቶም ያልሞከሩ አሁን ለመንግሥቱ መጽሐፍ ሽያጭ ወገባቸውን ሰብቀው ስለ አረመኔው  ሙብት ሲከራከሩ ይታያሉ ።

እነዚህ ግለሰቦች ከሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች በመንግሥቱ ለተገደሉ በመቆም ለፍርድ ይቅረብ ብለው ሲጠይቁ አልተሰሙም። ለዛች ጧሪ ላጣች አሮጊት እናት ፣ ለዛ ደጋፊ ላጣ አባት ጥብቅና ሳይቆሙ አሁን ለአረመኔው ሙብት በመቆም እርዳታ ማሰባሰብ መጀመራቸውን በተለያዩ ድረ ገፆች ለማንበብ ችለናል። ሌላው ቢቀር እንኳን ልጇ ለተገደለባት እናት የጥይት መግዣ ለከፈለችው አሮጊት ከዚህ ትርፍ አረመኔው ይመልስ ሲሉ አልተሰሙም።  በድህነቱ ምክንያት ለፍትህ የሚቆምለት አጥቶ በስቃይና በሞት አፋፍ ላይ ለሚገኘው ጧሪ ላጣው አባት ከመቆም ልጆቹን በድሎት አስተምሮ ዶክተር ላደረሰ አረመኔ መቆማቸው ዘግናኝ የፍትህ አድልኦ ነው ።

መንግሥቱ ኃይለማርያም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰው በደል ተዘርዝሮ የሚያበቃ አይደለም ። ወንጀሉም ይታወቃል፤ ተባባሪዎቹም በያሉበት ማንነታቸው ምስጢር አይደለም። አጼውን ጨምሮ የቀድሞ ባለስልጣኖችን፤ በርካታ መኮንኖችን፤ የደርግ አባላትን፤እነ ማርቆስ ሐጎስን ጨምሮ የሕዝብ ማህበራት መሪዎችን፤ እነ ጀኔራል ታደሰ ብሩንና አማን አንዶምን፤ ከሁለት መቶ ሀምሳ ሺ ያላነሱ ወጣትና አዛውንት ዜጎችን በነጻ እርምጃና ቀይ ሽብር፤ በግንባር የተሰለፉ ወታደሮችንና መኮንኖችን፤ አርሶ አደሮችን፤ እነ በዓሉ ግርማና ቄስ ጉዲናን፤ መፈንቅለ መንግስት ሞክሩ በሚል በርካታ ጄኔራሎችን የፈጀው፤ በአጠቃላይ አንድ ትውልድን የመተረውና ሀገርን ለገንጣዮች አመቻችቶ የሰጠው አላንስ ብሎት በአሁኑ ጊዜ መጽሐፍ በማሳተም ትርፍ ለማግበስበስና የስማዕትን ታሪክ ለማበላሸትና ደማቸውን ከንቱ ለማድረግ እየተራወጠ ይገኛል። ይህ ሀገራችንን ለወያኔ በመሸጥ ወደ ዚምባብዌ ሲሸሽ ሰብስቦ የሄደው ገንዘብ አልበቃው ብሎት አሁንም ይህንን የግፉን ክህደት የደረተበትን መጽሐፉን በመሸጥ በንፁሃን ደም አረመኔው መንግስቱ ሊያተርፍና ሊቀልድ ልንፈቅድለት አይገባም።

ለዛች የሚቆምላት ላጣች አሮጊት እናት ፣ ለዛ በእንባ ዓይኑ ለጠፋው አባት፣ ለዛ አባትና እናቱን ገድለው ብቻውን እንዲያድግ ለተደረገው ወጣትና መከራና ስቃይን እንዲቀበል ለተደረገው ዜጋ ሁሉ ልንቆም ልንሟገት ይገባል። ከአጠገባችን ወገኖቻችንን ሲገደሉ ያየን ፣ በታሪክ የሰማን ፣ ራሳችንም ስየል የተቀበልንና ይህ ግፍ መደገም የለበትም የምንል ሁሉ ዛሬ አንድ ላይ በመነሳት ለዚህ የግፍ ግፍ ማከተሚያ እጅ ለእጅ ተያይዘን ለተሰዉትና ታስረው ለተሰቃዩት ሁሉ ፍትህን መጠየቅ አለብን ።

በመሆኑም እኛ በዛ ሥርዓት ግፍ የደረሰብን ግለሰቦች ተሰባስበን ከመጽሐፉ የሚገኘው ገንዘብ በመንግሥቱ አሰቃቂ መንግሥት ልጆቻቸውን ፣ ባሎቻቸውን ፣ እህቶቸቸውን ገድሎ ካለ ጧሪ ለአስቀራቸው፣ ለሃገራቸው ሲዋደቁ አካላቸው ጎድሎ በየመንገዱ የወደቁ የኢትዮጵያ ጦር አባላት ገቢው እንዲውል በሕግ ለመጠየቅ በዝግጅት ላይ ነን። ተባበሩን እንላለንም ።

ይህንን በሚመለከት በደርግ መንግሥት ግፍ የደረሰባችሁ በሙሉ ከእኛ ጋር በመቆም ይህንን እኩይ ተግባር ለማከሸፍ በምናደርገው ጥረት ትተባበሩን ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን። በተለይም ደግሞ ለዚህ ተግባር የሚሆኑ ማናቸውንም ተጨማሪ መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ ስለሆነ በምስክርነት ፣ በጽሁፍ ፣ በፎተግራፍ ሊረዱ የሚችሉ ማናቸውንም ማስረጃዎች እያሰባሰብን ስለሆነ ትብብራችሁን እንጠይቃለን። ሀገርና ሕዝብን በአስከፊና አሰቃቂ ደረጃ ለበደለ አረመኔ ጠበቃ ሊሆኑ የተነሱትም የወንጀሉ ተባባሪ ናቸውና ሕዝብ ይፋረዳችዋል ። በኢትዮጵያ ህዝብ ደም መነገድ ሆነ መቀለድ በዝምታ የምናልፈው ወንጀል አይደለም።

**የወቅቱ ዋና የትግላችን ትኩረት በዘረኛው ወያኔ ላይ መሆን አለበት በሚል ያለፈውን አገዛዝ ግፍና ወንጀለኞች የረሳን የመሰላቸው በነሱው ብሶ ነጋ ጠባ በቁስላችን እንጨት ሲሰዱና ጸረ ወያኔውን ትግል ሊያድናቅፉ ሲራወጡ ዝም የምንል አለመሆናችንም መታውቅ አለበት።**

ከእኛ ጋር ለመገናኘት ከዚህ በታች ያለውን ኢሜይል ተጠቀሙ ።

redterrorvictims@gmail.com.

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !